አማራ ባንክ
AMHARA BANK
ከባንክ ባሻገር!
Beyond Financing!

**ለአማራ ባንክ አ.ማ ባለአክሲዮኖች በሙሉ**

**የባለአክሲዮኖች 4ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ**

በኢፌዲሪ የንግድ ሕግ አንቀፅ 366(1)፣ 367(1) እና 370 እንዲሁም በባንካችን መመስረቻ ጽሁፍ አንቀፅ 12.1.6 መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 9.1 መሰረት አማራ ባንክ አክሲዮን ማህበር የባለአክሲዮኖች 4ኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ቅዳሜ ህዳር 20 ቀን 2018 ዓ.ም ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት ጀምሮ በአዲስ አበባ ከተማ አዲስ ፓርክ ዴቨሎፐመንት ኃ.የተ.የግ ማህበር (ሚሊኒየም አዳራሽ) ይካሔዳል። በመሆኑም የተከበራችሁ የባንካችን ባለአክሲዮኖች በዕለቱ በጉባኤው ላይ እንድትገኙልን የአማራ ባንክ አ.ማ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያስተላልፋል።

1. ባንኩን የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች
1.1. የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት አድራሻ፡-
✓ አዲስ አበባ፣ ቂርቆስ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 8፣ ለገሃር መብራት - አምልድ ሕንጻ ከ16-25ኛ ፎቅ
✓ ስልክ: የጥሪ ማዕከል: 690 ፖ.ሳ.ቁ: 28450 ኮድ 1000
✓ ድረ ገጽ: https://amharabank.com.et/
1.2. የአክሲዮን ማህበሩ የምዝገባ ቁጥር፡- MT/AA/3/0052689/2014
1.3. የአክሲዮን ማህበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ብር፡- 7,416,250,000.00
1.4. የአክሲዮን ማህበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ብር፡- 7,416,250,000.00

**2. የመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች ፡-**
2.1. እ.ኤ.አ በ2024/25 የተደረጉ የአክሲዮን ዝውውሮችን ማፅደቅና አዳዲስ ባለአክሲዮኖችን መቀበል፣
2.2. እ.ኤ.አ የ2024/25 የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ማድመጥና ተወያይቶ ማፅደቅ ፣
2.3. እ.ኤ.አ የ2024/25 የባንኩን የውጭ ኦዲተር ሪፖርት ማድመጥና ተወያይቶ ማፅደቅ ፣
2.4. ተሻሽሎ በቀረበው የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና የምርጫ ፖሊሲ እና የአፈፃፀም መመሪያ ላይ ተወያይቶ ማፅደቅ፣
2.5 .እ.ኤ.አ የ2024/25 የትርፍ ድርሻ ድልድል እና ክፍፍልን በተመለከተ በዳይሬክተሮች ቦርድ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ማዳመጥና ተዋያይቶ ማፅደቅ፣
2.6 .የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን እ.ኤ.አ የ2024/25 ዓመታዊ የስራ ዋጋ እና እ.ኤ.አ የ2025/2026 ወርሃዊ አበል በሚመለከት በቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ተወያይቶ ማፅደቅ ናቸው።

**ማሳሰቢያ ፤-**

1. በጉባኤው ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ በተሰጠ ውክልና ወይም በንግድ ሕጉ አንቀፅ 377 መሰረት ጉባኤው ከሚካሔድበት ቀን 3(ሶስት) ቀናት በፊት በየትኛውም የባንኩ ቅርንጫፍ ማንነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ፣ ብሔራዊ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናውንና ኮፒ ይዘው በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በባንኩ የተዘጋጀውን ውክልና ቅፅ ሞልታቸው በመፈረም ተወካይ በመሾም በጉባኤው ተካፋይ ለመሆንና ድምፅ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን። ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ በተሰጠ ውክልና በጉባኤው ላይ የሚሳተፉ ተወካዮች በጉባኤው ቀን የውክልናውን ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ ይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል።
2. ሆኖም አንድ ባለአክሲዮን በባንኩ ጠቅላላ ጉባኤ በማንኛውም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ነው። እንዲሁም በስራ ላይ ያሉ የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና የባንኩ ሰራተኞች ዋና ስራ አስፈፃሚን እና ከፍተኛ ኃላፊዎችን ጨምሮ ባለአክሲዮኖችን በመወከል በብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር SBB/91/2024 አንቀፅ 20.3 መሰረት በጉባኤ ላይ መሳተፍ የማይችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን።
3. ባለአክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባኤው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ብሔራዊ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናውንና ፎቶ ኮፒ በመያዝ በጉባኤው ላይ መሳተፍ ይችላሉ። እንዲሁም ትውለደ-ኢትዮጵያውያን የሆኑ የውጭ የሐገር ዜግነት ያላቸው የባንካችን ባለአክሲዮኖች ትውልደ-ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቀኑ ያላለፈበት መታወቂያ (ቢጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እንገልፃለን።
4. ባለአክስዮኖች ባስመዘገቡት ተንቀሳቃሽ /ሞባይል ስልክ ቁጥር ላይ የባለአክስዮን መለያ ቁጥር የሚላክ በመሆኑ ባለአክስዮኖች ወይም ተወካዮች ባንኩ ባዘጋጀው ቅፅ ውክልና ለመስጠትም ሆነ ወደጉባኤው ሲመጡ ይህንኑ መለያ ቁጥር ይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል።
5. ድርጅትን ወክሎ የሚቀርብ ተወካይ የድርጅቱ/የማህበሩ ስራ አስኪያጅ መሆኑንና ድርጅቱን/ማህበሩን ወክሎ በጉባኤ ላይ ድምፅ ለመስጠት የሚያስችል ስልጣን ያለው ስለመሆኑ የሚያሳይ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት የተመዘገበ የመመስረቻ ፅሁፍ ወይም መተዳደሪያ ደንብ ወይም ቃለ-ጉባኤ በማስረጃነት ይዞ መቅረብ አለበት ፣ አልያም በባንኩ የውክልና ቅጽ መሰረት ውክልና የተሰጠው መሆን አለበት።
6. ባንኩ ባዘጋጀው ቅፅ ውክልና ለምትሰጡ ባለአክስዮኖች ሁሉም የባንኩ ቅርንጫፎች በስራ ቀናቶች የሚያስተናግዱ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን።

**ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥሮች +251115581461 ወይም +251115583593 ይደውሉ።**

**የአማራ ባንክ አ.ማ**
**የዳይሬክተሮች ቦርድ**